Lauf gegen Grenzen (የድንበር ወሰነን በመቃወም መሮጥ **)** ስደተኞችን በመደገፍ የሚደረግ የገቢ ማሰባሰቢያ ሩጫ ነው።

የውድድሩ አዘጋጆች " Verein gegen Grenzen ፣ ፈራይን ጌገን ግሬንዘን " እንዲሁም Freiplatzaktion Basel፣ ፍራይፕላትስአክስዮን ባዝል እና፣ አንላውፍስቴለ ፉር ሶን ፓፒር ባዝል Anlaufstelle für Sans-Papiers Basel በመተባበር ነው።

የሩጫ ውድድሩ በየአመቱ ባዝል ውስጥ የሚደረግ ሲሆን ማንኛውም ሰው መሳተፍ ይችላል። የዚህ ዝግጅት ዋና አላማ በማህበረሰቡ ውስጥ በስደተኞች ፖለቲካ ላይ ጥሩ ግንዛቤ ለማስረጽ ፣ የህዝብ ለህዝብ ግኑኝነትን ለማሳደግ እንዲሁም ይህን ላዘጋጁት ሁለት ድርጅቶች እና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመደገፍ የሚያስችል ገቢ ለማሰባሰብ ነው። የምንሮጠውም ብሩህ አይምሮ ለተሞላበት ማህበረስብ ፣ ለነቃ ማህበራዊ ተሳትፎ ፣ ከዘረኝነት ለፅዳች አለም እና መድሎ እና አድሎ የሌለብት የስደተኞች አያያዝ ነው።

ለመሳተፍ

በዝግጅቱ ላይ ለመሳተፍ ለሚፈልግ ሁሉ ሰው ክፍት ሲሆን ። እርሶም በሩጫው ላይ በመሳተፍ ወይም በገዘብ መዋጮ መርዳት ይችላሉ። ከፈለጉም በዝግጅቱ ላይ የራስዎን ቦታ ይዘው ወይም በእንግድነት መሳተፍ ይችላሉ።

እንደ ሯጭ ለመሳተፍ

በሩጫው ለመሳተፍ ከፈለጉ በድርጅታችን ድህረገጽ(www.laufgegengrenzen.ch) ላይ በቀጥታ መመዝገብ የሚችሉ ሲሆን ወይም የእለቱ ቀን መረጃ መስጫ ቦታው ጋ በመሄድ ተመዝግበው መወዳደር ይችላሉ። ምዝገባው በነጻ ሲሆን ቁጥር ተቀብለው ቀጥታ በውድድሩ መሳተፍ ይችላሉ።

አንድ የሩጫ ውድድር 45 ደቂቃ የሚፈጅ ሲሆን ፣ በዚህ ግዜ ውስጥም እርሶ የቻሉትን እና የፈቀዱትን ያህል ዙር መሮጥ ይችላሉ። አንድ ዙር ለመጨረስ 300 ሜትር ያክል መሮጥ ይጠበቅብዎታል። የህጻናት ሩጫንም አካተናል ፣ አንድ ዙር 150 ሜትር ሲሆን 20 ደቂቃ ይፈጃል። በሚሮጡበት ወቅት ምን ያህል ዙር እንደሮጡ መቁጠር አይጠበቅብዎትም የሮጡትን ዙር የሚቆጥሩ ሰዎች አዘጋጅተናል።

በየአንዳንዱ ዙር ልክ መጠን ገንዝብ ይኖራል ፣ ይህንንም ለማሳካት እያንዳንዱ ተሳታፊ በገንዘብ ሊያግዘው የሚችል ሰው ወይም ስፖንሰር ማፈላለግ ይኖርበታል። ይህም ማለት ለምሳሌ ፡- ጉዋድኛ ፣ የስራ ባልደረባ ፣ ድርጅቶች እንዲሁም የቅርብ ዘመድ ወይም የሚያውቁት ሰው ሊሆን ይችላል።

እርግጥ ነው ምንም እንኳ በገንዘብ የሚረዳዎ ሰው ባያገኙም በውድድሩ ላይ መሳተፍ ይችልላሉ። በውድድሩ መጨረሻም ለፈጣኑ ሯጭ እና ብዙ ገንዘብ መሰብሰብ ለቻለው ተወዳዳሪ ሽልማት ይኖራል።

በገዘብ መዋጮ ላይ ለመሳተፍ

እያንዳንዱ ተሳታፊ በገንዘብ የሚደግፈው ሰው በማፈላለግ ለሮጠው/ችው የዙር መጠን ያህል የተወሰነ የገንዘብ መጠን እንዲከፍለው ይጠይቃል። የገንዘቡ መጠን የፈለገውን ያህል ቢሆን ችግር የለውም። ምንም ያህል ዙር ቢሮጥ የቻሉትን ያህል ቢከፍሉ ችግር የልውም። እያንዳንዱ ተሳታፊ በምዝገባ ወቅት በገንዘብ የሚያግዙትን ሰዎች ስም ዝርዝር እንዲያመጣ ይጠበቅበታል።

በመጨረሻም የሮጡትን ዙር በመቁጠር ስፖንሰሮ ምን ያህል መክፈል እንዳለባቸው በገቡት ቃል መሰረት ይሰላል። በመቀጠልም ለስፖንሰሮ የክፍያ ደረሰኝ በቀጣዮቹ ሳምንታት ይላክላቸዋል።

ሁሉንም ገንዘቦች ሰብስበን ካስገባን በሁዋላ ፣ የተሰበሰበው ገንዘብ ለሁለቱ አዘጋጅ ድርጅቶች እና ለሌሎች በስደተኞች ዙሪያ ላይ ለሚሰሩ ፕሮጀክቶች ይከፋፈላል። ከተሰበሰበው ገንዘብ ውስጥ 1/3 ኛ ያህሉ ገንዘብ ለ ፍራይፕላትስአክሲዎን ባዝል (Freiplatzaktion Basel) ገቢ ይደረጋል እንዲሁም ሌላ 1/3 ኛ ያህሉ ገንዘብ ለ አንላውፍሽተለ ፉር ሶን ፓፒር ባዝል (Anlaufstelle für Sans-Papiers Basel) ገቢ ይደረጋል። የተቀረው 1/3 ኛ ገቢ ደግሞ ለሌሎች ትናንሽ ፕሮጀክቶች የሚሰጥ ይሆናል። ከዝግጅቱ ፍጻሜ በሁዋላ ማንኛውም ሰው ፕሮጀክቶችን መጠየቅ ይችላል።

Contact

info@laufgegengrenzen.ch (German, English, French, Spanish, Portuguese)

---

* ሁሉንም ጾታ በ እኩል ያሳትፋል